# የኮቪድ 19 ክትባቶች ጉዳት አልባ ነውን?

- ክትባቶች ህይወትን ለማዳን ፣ የሚወዷቸውን ሰዎች ለመጠበቅ እና ሁሉም ወደ መደበኛ ሁኔታው እንዲመለስ ከሚረዱ እጅግ ውጤታማ እና ጉዳት አልባ ዘዴዎች አንዱ ነው ፡፡
- ሁሉም አበይት የሕክምና ጥናት የሚያሳዩት፤ የፒፊዘር (Pfizer) እና የሞዴርና (Moderna) ክትባቶች ጉዳት አልባ እና ውጤታማ መሆናቸውን ነው።
- የፋይዘር (Pfizer) እና ሞደርና (Moderna) ክትባቶች በምግብ እና መድሃኒት ቁጥጥር አስተዳደር (ኤፍ/ዲ/ኤ) ይሁንታ ያገኙ ናቸው፤ ደግሞም ከ40,000 በላይ ተሳታፊዎችን ባቀፈ የክሊኒክ ሙከራ ምርመራ ያለፉ ሲሆን፥ ከ ከእነዚህም ውስጥ ከ40% በላይ የሚሆኑት ከተለያዩ ህብረተስብ የተውጣጡ ናቸው፡፡



- ክትባቶቹ በፍጥነት የተዘጋጁ ሲሆን፣ ይህም አንዳንድ ሰዎችን እርግጠኛነት እንዳይሰማቸው ያደርጋቸዋል፡፡ ሣይንቲስቶች ስለኮሮናቫይረስ ለ50 ዓመታት ሲመራመሩ ቆይተዋል፤ ደግሞም በ2002 ከተፈጠረው የሳርስ ወረርሽኝ ጀምሮ ክትባት ለማግኘት ሲጥሩ ነበረ፡፡
- የኮቪድ 19 ክትባትን ወስደው ከባድ የሆነ ያልተገባ ስሜት ሊሰማዎት የሚችልበት ዕድል በጣም አነስተኛ ነው፥ እንደውም ከ1% በታች፡፡ መድሃኖቶችን ሲወስዱ አለርጂ ይገጥምዎት ከነበረ የግል ሐኪምዎን ያነጋግሩ፡፡
- አነስተኛ የሆኑ የጎንዮሽ ጉዳቶች ለምሣሌ የክንድ አከባቢ ህመም ወይም ጊዜያዊ ራስ ምታት ወይም ትኩሳት ሲኖር ለወደፊት ኢንፌክሽኖችን ለመከላከል ሰውነታችን የሚያደርገውን የመከላከያ ሥርዓት ግንባታ ተከትሎ የሚፈጠሩ ጤናማ ምልክቶች ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች በጥቂት ቀናት ውስጥ ይጠፋሉ ፡፡
- የህክምና ባሞያዎች እንደሚመክሩት፥ ነፍሰጡር እና ጡት የሚያጠቡ ሴቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የአሁኑን የኮቪድ-19 ክትባት በደረሳቸው ጊዜ መውሰድ አለባቸው፡፡

ስለክትባት ደህንነት፣ ስለውጤታማነት፣ ስለመገኘቱ እና ስለሕጋዊነቱ ይበልጥ ለመረዳት የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡፡

2.5.21

**ALEXANDRIAVA.GOV/VACCINES**